የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስባተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ኅዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፫ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 3
ADDIS ABABA 1st December, 2010

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፫/፪ሺ፫ ዓ.ም

የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ አዋጅ .....ገጽ ፩ሺ፮፻፸

ማረሚያ ቁጥር ፯/፪ሺ፫.....ገፅ ፩ሺ፮፻፸፪

CONTENTS

Proclamation No. 693/2010

Income Tax (Amendment) Proclamation .....Page 5670

Corrigendum No. 7/2010 .....Page .5672

አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፫/፪ሺ፫

የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፯/፲፱፻፺፬ /እንደ ተሻሻለ/ እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፫/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ማሻሻያ

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፯/፲፱፻፺፬ /እንደተሻሻለ/ ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ /፲፯/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፲፯/ ተጨምሯል፡-

'፲፯ "ንፋስ አመጣሽ ገቢ" ማለት ማንኛውም ሰው በራሱ ጥረት ሳይሆን በአገር ወይም በዓለም ዐቀፍ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ በተፈጠረ ለውጥ ምክን ያት ያገኘው ገቢ ሲሆን፣ ዝርዝሩ ሚኒስ ትሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰ ናል።'

PROCLAMATION NO. 693/2010.

A PROCLAMATION TO AMEND THE INCOME TAX PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Income Tax (As Amended) Proclamation No. 286/2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub article (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Income Tax (Amendment) Proclamation No.693 /2010."

2. Amendment

The Income Tax (As Amended) Proclamation No. 286/2002 is hereby amended as follows:

1/ The following new sub-article (17) is added after sub-article (16) of Article 2 of the Proclamation:

'17. "Windfall Profit" means profit obtained by any person as a result of a change occurred in local or international economic and political situations without its own efforts, particulars shall be determined by the directive of the Minister to be issued.'

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2 -30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፴፯ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፰ ተጨምሯል፡-

"፴፰ <u>ንፋስ አመጣሽ ገቢ</u>

፩/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ከተመለከቱ የንግድ ሥራዎች የሚገኝ ንፋስ አመጣሽ ገቢ በመመሪያው በተመለከተው የማስከፈያ ልክ ግብር ይከፈልበታል።

፪/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ፡-

ሀ/ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ነው ሊባል የሚችለውን የገቢ መጠን፤

ለ/ በንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ በዚህ አንቀጽ የተጣለውን ግብር ሊከፍሉ የሚገባቸውን የንግድ ሥራዎች ዓይነት፤

ሐ/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈለው ግብር ሥራ ላይ የሚውልበትን ቀን፤

መ/ የግብር አወሳሰኑን ዘዴና ለግብሩ አወሳሰን መሠረት የሚሆኑ ታሳቢዎችን፤

እንዲወስን ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፫/ ሚኒስትሩ የንግድ ሥራ ባህሪያትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለተለያዩ የንግድ ሥራዎች ንፋስ አመጣሽ ገቢ የሚባለው የገንዘብ መጠን እንዲለያይ ለማድረግ እንዲሁም የተለያየ የግብር ማስከፈያ ልክ ለመወሰን ይችላል።"

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፵፩ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፫/ ተጨምሯል፡-

"፫ ባንኰች ንብረት በዋስትና በመያዝ ብድር ከመስጠታቸው በፊት ለዋስትና የቀረበው ንብረት ባለቤት አስቀድሞ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሚፈለግበትን ግብርና ቀረጥ የከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።"

፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ /መ/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /ሠ/ ተጨምሯል፡-

"ሠ. ለኢኮኖሚ፣ ለማኅበራዊ ወይም ለአስተዳደር ምክንያቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ሊከፈልበት የሚገባው ገቢ ከግብር ነፃ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።"

2/ The following new Article 38 is added after Article 37 of the Proclamation:

" 38. <u>Windfall Profit</u>

1/ Windfall Profit obtained from businesses prescribed in a directive to be issued by the Minister shall be liable to tax at a rate to be determined in such directive.

2/ The Minister is empowered to prescribe by a directive:

a) the amount of income to be considered as windfall profit;

b) businesses that are subject to tax levied under this Article on windfall profit;

c) the date on which the tax shall become effective;

d) the manner in which the tax is assessed and factors that need to be taken into consideration.

3/ The Minister may, taking into consideration the nature of the business, prescribe different amounts to be considered as windfall profit and rates for different types of businesses."

3/ The following new sub-article (3) is added after sub-article (2) of Article 41 of the Proclamation:

"3. Banks shall, before accepting a property as collateral for a loan, ensure that the owner of the property, if previously engaged in business activities has fulfilled its tax obligations."

4/ The following new sub-article (e) is added after sub-article (d) of Article 42 of the Proclamation:

"e. may exempt any income taxable under this Proclamation for economic, administrative or social reasons."

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፮ ተሽሮ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፩፻፮ ተተክቷል፡-

"፩፻፮ መቀጫን ስለማንሳት

፩/ በግብር ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንደሁኔታው አግባብ ባለው ኃላፊ ወይም በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ በሙሉ ወይም በከፊል ሊነሳ ይችላል።

፪/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር በሚያወጣው መመሪያ መቀጫው የሚነሳበትን ሁኔታ እና በየደረጃው ባሉ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ኃላፊዎች እና በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊነሳ የሚችለውን የመቀጫ ገንዘብ መጠን ይወሰናል።"

፮/ ከአዋጁ አንቀጽ ፴፰ እስከ ፩፻፳ ያሉት አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፴፱ እስከ ፩፻፳፩ ሆነው ተስተካክለዋል።

፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

ማረሚያ ቁጥር ፯/፪ሺ፫

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀፅ ፴፰ "ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ከአንድ አመት በኋላ ጀምሮ የፀና ይሆናል።" የሚለው "ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።" ተብሎ ይነበብ።

5/ Article 106 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 106:

"106. Waiver of Penalty

1/ Administrative penalty imposed on a taxpayer may be waived by the relevant official of the Tax Authority or the Review Committee, as appropriate, in accordance with the directives to be issued by the Revenue and Customs Authority.

2/ The Director General of the Revenue and Customs Authority may by a directive prescribe the conditions under which the administrative penalty may be waived, and the amount of penalty that officials of the Authority and the Review Committee are authorized to waive."

6/ Articles 38 to 120 of the Proclamation are renumbered from Article 39 to 121 consecutively.

3. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 1st day of December, 2010

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

Corrigendum No. 7/2010

Article 38 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia which reads "This Proclamation shall come into force a year after its publication in the Federal Negarit Gazeta." is hereby corrected and shall be read as "This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta."